# ‘’ባዶ!’’ አለ ገሞራው

ከጌትነት

ያ ትልቁ ጠቢብ፣ ገሞራው እንዳለን፣
ዜሮ ቁጥር ላይሆን፣ በከንቱ መማሰን!

ቢቃጠል ሆቴሉ!
ቢነቀል ሐውልቱ!
ቢነድ ደን ቅጠሉ!
የቼብሃ ዛፍ ነው፣ ሁሉም መሠረቱ፣
አይቀርም ሐቅ ነው፣ ዳግመኛ መምጣቱ!
ሲጠፉ አጥፊዎቹ! እሱ መታየቱ!
ደምም ቢንቆረቆር!
አጥንት ቢሰባበር!
ስጋ በጭካኔ ቢከተፍ! ቢመተር!
ይህ ሁሉ ህያው ነው፣ ቆሞ እሚያኖር ሀገር!




ሰማዕት ሁሌ ሲኖር፣ ገዳይ ጥሎ ያልፋል!
ታሪክና ትውልድ፣ ዘላለም ይኖራል!
የገፋውን ጥሎ፣ ተገፊ ይነሳል!
ወሳጆች ሲሄዱ፣ የሄደው ይመጣል!
ሰው ሰራሽ ድንበሩም፣ በነበር ይጸድቃል!
በእንጨት የታነጸው፣ በድንጋይ ይጸናል!
ሹም ባሽ የባንዳ ልጅ! ዋጋውን ይከፍላል!
ባነደደው እሳት፣ ራሱ ይጋያል!
እንጂ የጣይቱ፣ እሳት መች ይጠፋል!



የጴጥሮስም መንፈስ፣ ቅኔውን ይዘርፋል፣
‘’እናንት ቀሳውስት፣ አቤት ሲያምርባችሁ!
‘’ስታድኑ አየሁኝ፣ ሰው በመስቀላችሁ!’’
እያለ ስለ ሃቅ፣ ሃቅን ይዘምራል!

ባንዳ የባንዳ ልጅ፣ በከተማው ነግሶ፣
ያጠፋ ቢመስለው፣ ቤት እሳት ለኩሶ፣
ያወጣ ቢመስለው፣ ሀውልቱንም ምሶ፣
ይመጣል በጊዜው፣ ሁሉም ተመልሶ!

ባዶማ ባዶ ነው! ከምኑ ይጣፋል!
አገር ባላገሩ ባዶን በአንድ ይተካል!!

ጃንዋሪ 12. 2015